የኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና
ማህበራት መድረክ
Ethiopian Charities and Societies Forum

**ቁጥር:** 0321/ECSF/2008
**ቀን፡** 11/08/2008

## በጋምቤላ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በንፁሃን ዜጎቻችን ላይ የተፈፀመውን ግድያና አፈና በተመለከተ ከኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት መድረክ የተላለፈ የሀዘን መግለጫ

የኢትዮጵያ የፌደራል የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት መድረክ ግንቦት 2005 ዓ.ም የተቋቋመ በኢትዮጵያ በፌደራልና በክልል የሚገኙ ኢትዮጵያዊ፣ የኢትዮጵያ ነዋሪዎች እና ዓለምአቀፍ የበጐ አድራጐት ድርጅቶች እና ማህበራትን በአባልነት ያቀፈ የጋራ ሕጋዊ መድረክ ነው፡፡

ይህ መድረክ ሚያዚያ 7 ቀን 2008 ዓ.ም. በጋምቤላ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ውስጥ በሚገኙ ሶስት ወረዳዎች ከደቡብ ሱዳን በመጡ የታጠቁ ሃይሎች በንፁሃን ዜጐቻችን በተለይም በሕፃናት እና ሴቶች ላይ የተፈፀመው የግድያና አፈና በኢትዮጵያ ውስጥ በፌደራልና በክልል ደረጃ እየሰሩ የሚገኙ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ከመላ ሠራተኞቻቸው ጋር በመሆን የተሰማቸውን ጥልቅ ልባዊ ሀዘን እየገለፁ፤ ይህንን ኢ-ሰብአዊ ተግባር በአፅንኦት ያወግዛሉ፡፡

ጥቃቱን የፈፀሙ አካላትን ተከታትሎ ታፍነው የተወሰዱትን ህፃናትና እናቶችን ለማስመለስ በሚደረገው ጥረት አጋርነታችንን እየገለፅን፤ ለሟች ቤተሰቦች፣ ለመንግስትና ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ መፅናናትን እንመኛለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

ነጋሽ ተክሉ
ሊቀ መንበር

Tele: 0118699908
P.O.Box:24366/1000
E-mail: info@fcsf.net
Fax: 0116638127